ቴዎድሮሳዊያንና ትምህርቶቻቸው

የቴዎድሮሳውያን ትምህርት በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ ሲመዘን የተገኙ መሠረታውወ ስህተቶች

1. ቁርባን ተቀበሉ አልተባልንም
2. ክህነት የለም/ አንድ ካህን ፓትርያርኩን ስላወገዙ
3. ትምህርታቸውን በትንቢት ላይ ብቻ መመሠረት/ማመካኘት
4. የትንቢቱን ምንጭ ሲጠየቁ በበረኻ አባቶተች ማመካኘት
5. ቴዎድሮስን በተመለከተ የሚያስተምሩት
6. ቤተ ክርስቲያ ያላስተማረችው የመጻን ምልክት
7. ክርስቲያኑን ሳይቀር የነሱን ምልክት ካልያዘ ማጥፋት
8. ስለ አብያተ ክርስቲያናት ያላቸው አስተምህሮ
9. ስለኢትዮጵያ ያላቸው አስተምህሮ
10. ዋና ዋና ጥቅሶቻቸውና አጋዥ መጻሕፍቶቻቸው

1. ቁርባን ተቀበሉ አልተባልንም

- “እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ የምትፈልጉኝ እንጀራን ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ ነው እንጂ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም። ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘለዓለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ ... የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ በእኔ የሚያምንም ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም። ...

- “የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ፣ ሞቱም፣ ሰው ከእርሱ በልቶ አንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው። ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘለዓም ይኖራል። እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።”

ዮሐ. 6:26-27 ፣ 35:49-51

- “ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ፣ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፥- እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖ ሰጣቸው፤ እንዲህም አለ፥- ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎችም ኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።”

ማቴ. 26:26-28

በቁርባን የሚገኙ ሀብታት

1) የዘላለም ሕይወት

“ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።

ዮሐ. 6፡53-56

- 2) ከክርስቶስ ጋር የፀጋ ተዋሕዶ
- “ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።”

ዮሐ. 6፡53-56

3) የኃጢአት ይቅርታ እናገኛለን

- “ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎችም ኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።” ማቴ. 26:26-28
- “ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፥ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።”

1 ዮሐ. 1፡7

- 4) ሞቱንና ትንሣኤውን እናስባለን፣ እንመሰክራለን
- “ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።”

1 ቆሮ. 11፡26

5) ኃጢአትን ለማሸነፍ ኃይልና ጉልበት እናገኛለን

“ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።”

ፊል. 4፡13

- “ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።” ገላ. 2፡20

ም. ቁርባን ራሱ በጸሎተ ሐሙስ ጌታ የፈጸመው ምሥጢር ነው።
በየቅዳሴው ጊዜ የሚፈጸመው ያው ምሥጢር ነው።
የሚደጋገም አይደለም፣ ያው ራሱ የምሴተ ሐሙሱ፣ ጌታ
በዕለት ዓርብ የፈጸመው ነው እንጂ።

ምሥጢረ ቁርባን በአበው ትምህርት

- “. . . ሀበነ ሥጋከ ወደመከ ዘወሀብኮሙ ለአርዳኢከ . . . ጎብስተ ሕይወት ጎብስተ መድኃኒት ዘወረደ እምሰማያት በዘይሠረይ ኃጢአት . . . - ለደቀ መዛሙርትህ እንደ ሰጠሃቸው ለእኛም ቅዱስ ሥጋህንና ክቡር ደምህን ስጠን፣ . . . ኃጢአት በሚሠረይበት ገንዘብ ከሰማያት የወረደ የሕይወት ጎብስትና መድኃኒት ነው . . .”

(ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘቅዱስ ቴዎድሮስ)

- “ከቅዱስ ቁርባንና ከጸሎት ይርቃሉ፤ ምክንያቱም በምሥጢረ ቁርባን የሚቀርበው ጎብስት ስለ እኛ ኃጢአት መከራ የተቀበለውና ከሞት የተነሣው የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ መሆኑን አያምኑምና ነው። ስለዚህ በዚህ ታላቅ የእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የማይገባ ነገር የሚናገሩ ሰዎች እነርሱ በክርክራቸው መካከል ሞትን በራሳቸው ላይ ያመጣሉ (እየተከራከሩ ሳሉ ይሞታሉ)።
-

- “ወረደ ወልድ እምሰማያት ወተወልደ በተድላ መለኮት ወቦአ ውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ወቦአ ውስተ ይእቲ ማዕድ ደመረ ሥጋሁ ውስተ ዝንቱ ጎብስት ወከዓወ ደሞ ውስተ ዝንቱ ጽዋዐ መድኃኒት ወዲያቆንሰ ዘንተ ርእዮ አንከረ ሀለው ካህናት ውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ እምዝንቱ ጎብስት ወ. ወሀቡ ለሕዝብ እንዘ ትብሉ ሥጋሁ ለክርስቶስ አሜን ይበል ዘይትሜጦ ወ. ዘኒ ጽዋዐ ሀቡ እንዘ ትብሉ ደሙ ለክርስቶስ አሜን አሜን ይበል ካዕበ ዘይትሜጦ ወ. መንክር ግብር ወዕፀብ ዘተገብረ ሥጋሁ ቅዱስ መብልዓ ጽድቅ ለሰብእ ዘረሰዮ ለሥርየተ ኃጢአት . . . - ወልድ ከሰማያት ወረደ፣ በመለኮት ክብር ተወለደ፣ ወደ መጋረጃው ውስጥም ገባ፣

- ወደዚህች ማዕድም ገባ፣ ሥጋውን ከዚህ ጎብስት ጋር አንድ አደረገ፣ ደሙንም በዚህ በመድኃኒት ጽዋ ውስጥ አፈሰሰ (ጨመረ)፤ ይህን የተመለከተ ዲያቆንም [ቅዱስ እስጢፋኖስ] አደነቀ። ካህናት በመጋረጃው ውስጥ አሉ፤ እነርሱንም ጌታችን እንዲህ አላቸው፡- ‘ከዚህ ጎብስት ብሉ፣ ለሕዝቡም ‘ይህ የክርስቶስ ሥጋ’ ነው እያላችሁ ስጡ፤ ሥጋውን የሚቀበለውም ‘አሜን’ ብሎ ይቀበል። ይህን ጽዋም (ደሙን) ‘ይህ የክርስቶስ ደም ነው’ እያላችሁ ስጡ፣ የሚቀበለውም ‘አሜን አሜን’ ብሎ ይቀበል። እጅግ በጣም አስደናቂና አስገራሚ ነገር ተደረገ፤ ይኸውም ቅዱስ ሥጋው ለሰዎች እውነተኛ ምግብና የኃጢአታቸው ማስተሥረያ መድኃኒት ሆኖ የመሰጠቱ ነገር ነው።”

(ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘቅዱስ እስጢፋኖስ)

- “ነገር ግን በአክብሮት ቢመለከቱትና ቢያምኑበት ይሻላቸው ነበር። ስለዚህ እንደዚህ ካሉት ሰዎች ትርቁ ዘንድ የተገባ ነው፣ ከእነርሱ ጋርም በግልም ሆነ በማኅበር ግንኙነት አይኑራችሁ።”

ቅዱስ አግናጥዮስ

- “ታላቁ ጸሎትና አስተብቁዖታት ወደ እግዚአብሔር ከተደረገ በኋላ **ቃል** በጎብስቱና በጽዋው ላይ ይመጣል፣ እነርሱም [ጎብስቱና በጽዋው ያለው ወይን] የእርሱን ቅዱስ ሥጋና ደም ይሆናሉ።” **ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ**

- “በምሥጢረ ቁርባን የሚቀርቡት ኅብስቱና ወይኑ ቅዱስና ገናና የሆነውን ስመ ሥላሴን ከመጥራታችንና ከመማጸናችን በፊት ተራ ኅብስትና ወይን እንደ ነበሩ ሁሉ፣ ከጸሎተ ቅዳሴው በኋላ ግን ኅብስቱ የክርስቶስ አካል ይሆናል፣ ደሙም የክርስቶስ ደም ይሆናል።”

ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም

- “. . . እጅግ የተከበርህ ወዳጄ ሆይ፣ እግዚአብሔር ቃልን በጸሎትህ ስትጠራውና ያለ ሥለት በሆነ ሁኔታ የጌታችንን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በምትፈትትበት ጊዜ ስለ እኔ መጸለይንና መማለድን አታቋርጥ።”

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ መልእክት ፡ነበ አምፊሎቅዮስ ጳጳስ ዘኢቆንዮን

- “ቅዱስ ጳውሎስ ያስተማረው ትምህርት ብቻ እንኳ እነዚያን አምላካውት ምሥጢራት በተመለከተ ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች መሆን እንድትችሉ ለማድረግ በራሱ በቂ ነው። ግልጽ በሆነ ሁኔታ እንዲህ ሲል ሰምታችሁታልና፥- ‘ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተላልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፥ ቆርሶም እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ሥጋዬ ነው አለ፤ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ ካመሰገነ በኋላ ይህ ደሜ ነው፣ እንካችሁ ጠጡ አላቸው።’ እንግዲህ እርሱ ራሱ ባለቤቱ ጎብስቱን ‘ይህ ሥጋዬ ነው’ ብሎ ከተናገረና ካወጀ ይህን ሊጠራጠር የሚችል ማን አለ? እንዲሁም እርሱው ራሱ በማይታበል ቃሉ ‘ይህ ደሜ ነው’ ብሎ በግልጽ የተናገረውን ‘አይ የእርሱ ደም አይደለም’ ብሎ ማን ሊያመነታና ሊጠራጠር ይችላል? **ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም**

መሥዋዕት

- ስለሆነም በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ የሚቀርበው መሥዋዕት ሌላ ወይም አዲስ መሥዋዕት ሳይሆን ጌታችን አንድ ጊዜ የፈጸመውና በዕለተ ዓርብ የቆረሰው ሥጋውና ያፈሰሰው ደሙ ነው፤ በየጊዜው በየቤተ ክርስቲያኑ በጸሎተ አኮቴት የሚከብረውና የሚለወጠው የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ከዚያች ከዕለተ ዓርብ ጋር የሚገናኝና አንድ የሚሆን ነው ማለት ነው።
- የእያንዳንዱ ጸሎተ ቅዳሴ ፈጻሚውና ቀዳሹም ራሱ ጌታችን ነው።

- እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ስለ ከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው፤ እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። ቅዱስና ያለ ተንኮል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ፥ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባልና፤

- “እርሱም እንደነዚያ ሊቃነ ካህናት አስቀድሞ ስለ ራሱ ኃጢአት በኋላም ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት መሥዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም፤ ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጎአልና። ሕጉ ድካም ያላቸውን ሰዎች ሊቀ ካህናት አድርጎ ይሾማልና፤ ከሕግ በኋላ የመጣ የመሐላው ቃል ግን ለዘላለም ፍጹም የሆነውን ልጅ ይሾማል።” ዕብ. 7፥ 23-28

- “እንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነጻል፥ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም። እንግዲህ በሰማያት ያሉትን የሚመስለው ነገር በዚህ ሊነጻ እንጂ በሰማያት ያሉቱ ራሳቸው ከእርሱ ይልቅ በሚበልጥ መስዋዕት ሊነጹ የግድ ነበረ። ክርስቶስ በእጅ ወደ ተሰራች፥ የእውነተኛይቱ ምሳሌ ወደ ምትሆን ቅድስት አልገባምና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ አሁን ይታይ ዘንድ ወደ እርሰዋ ወደ ሰማይ ገባ።

- “ሊቀ ካህናትም በየዓመቱ የሌላውን ደም ይዞ ወደ ቅድስት እንደሚገባ፥ ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ አልገባም፤ እንዲህ ቢሆንስ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር፤ አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል። ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፥ እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ፥ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሰዋ በኋላ፥ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል።”
- ዕብ. 9፥25-28

- በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል። ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞአል፤ እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ፥

- “. . . የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ፥ ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢአት ማቅረብ የለም።

ዕብ. 10፡10-12፣ 18

- ስለዚህ እኛ ከአሁን ጀምሮ ማንንም በሥጋ እንደሚሆን አናውቅም፤ ክርስቶስንም በሥጋ እንደ ሆነ ያወቅነው ብንሆን እንኳ፥ አሁን ግን ከእንግዲህ ወዲህ እንደዚህ አናውቀውም።

- ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።

- ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤

- እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ።

- እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን።

የቅዱስ ቁርባን መሥዋዕትነት በቀደምት አበው ትምህርት

“ሀበነ ንንሣእ ወንትመጦ እምዝንቱ ኅብስት ሥጋከ ውእቱ ዘወረደ እምሰማያት ዘሐዳስ ሥርዓት . . . - የሐዲስ ሥርዓት መሥዋዕት ይሆን ዘንድ ከሰማይ የወረደውንና ቅዱስ ሥጋህ የሆነውን ይህን ኅብስት እንቀበል ዘንድ መስጠትን ስጠን”

(ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘአቡነ አረጋዊ)

- “ታዲያ ይህ ምንድን ነው? በየቀኑ መሥዋዕት አናቀርብምን? አዎ፣ በርግጥም እናቀርባለን፤ ሆኖም የምናቀርበው መሥዋዕት ሞቱን በማሰብ ነው፣ ይህ መሥዋዕትም አንድ ነው እንጂ ብዙ አይደለም። ብዙ ያይደለ አንድ የሚሆነው እንዴት ነው? ያ መሥዋዕት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደ ተሠዋና ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ እንደ ገባ ይህም ያን ጊዜ ያቀረበውን መሥዋዕት ያንኑ ነው እንጂ ሌላ ወይም አዲስ መሥዋዕት አይደለም።

- ሁል ጊዜ የምናቀርበው መሥዋዕት ያው አንድ ነው እንጂ ዛሬ አንድ በግ ነገ ደግሞ ሌላ በግ አይደለም፤ ሁል ጊዜ፣ ዛሬም ነገም አንድ ነው እንጂ፤ ስለዚህም መሥዋዕቱ ያው አንድ ነው። እንዲህ ሆኖም ግን አሁንም መሥዋዕቱ በተለያዩ ቦታዎች (ቤተ ክርስቲያናት) ስለሚቀርብ ብዙ ክርስቶሶች አሉን? በጭራሽ! በየትም ቢሆን ክርስቶስ አንድ ነው፤ እዚህም በፍጹም ሙሉነት በእርሱነቱ አለ፣ እዚያም እንዲሁ እርሱው ራሱ እንበለ ሕጸት አለ፣ አንድ አካል።

- ስለሆነም በተለያዩ ቦታዎች ቢሠዋም አንድ አካል ነው እንጂ ብዙ አካል እንዳይደለ ሁሉ፤ እንደዚሁም እርሱ አንድ መሥዋዕት ነው። እኛን የሚያነጻንን መሥዋዕት ያቀረበው ሊቀ ካህናታችን እርሱ ነው። እና ዛሬ የምናቀርበው መሥዋዕት ያን ጊዜ የቀረበውን መሥዋእት ነው፣ በየጊዜው ቢቀርብ አያልቅም። በየጊዜው የምናቀርበው መሥዋዕት ሌላ መሥዋዕት አይደለም፣ ሁል ጊዜ የምናቀርበው ያንኑ መስዋዕት ነው እንጂ::"

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ዕብራውያን

“ጌታችን ተሰውቶ በምሥዋው (በታቦቱ) ላይ ተኝቶ ስታየው፣ ካህኑ ቆሞ በመሥዋዕቱ ላይ እየጸለየ ስትመለከተው፣ ምእመናን ሁሉ በዚያ በከበረው ደሙ እየተነዙ ስታይ፣ ከሰዎች መካከል እንዳለህ ታስባለህን? በምድር ላይ ያለህ ይመስልሃን?

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ በእንተ ክህነት፣ መጽሐፍ 4

2. ክህነትን በተመለከተ

- 2.1 ክህነት ምንድነው?
- የክህነት መዝገበ ቃላታዊ ትርጉም፡-
- የክህነት ሥርወ ቃል ተክህነ አገለገለ ከሚል የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ።ፍቺውም ሲብራራ ካህን መኾን ክህነት ተሸሞ በግዜር ፊት ቁሞ ማገልገል፣ የአምልኮ ሥራ መሥራት ስለራስና ስለሕዝብ መሥዋዕትና ጸሎት ማቅረብ መባረክ መቀደስ ማጥመቅ ማቁረብ ማለት ይሆናል።

2. ክህነትን በተመለከተ

- ከዚህም በመነሣት ተያያዥ የሆኑት ቃላት እደሚከተለው ይተረጉማሉ።
- ካህን፡- በቁሙ ዲያቆን፣ ቄስ፣ ጳጳስ የእግዚአብሔር አገልጋይ የሕዝብ መሪ አስተማሪ መንፈሳዊ አባት።
- ክህነት፡- መካን ማስካን ካህንነት ተክኖ ማገልገል አገልግሎት መንፈሳዊ ሹመት ሦስት ዕርከኖች ያሉት። ሦስቱ ላይኞች ጳጳስና ቅስና ዲቁና አራ ታችኞች ንፋቅ ዲያቆን አንባቢ መዘመርና በረኛ/አጻዌ ኖሕት/።

2. ክህነትን በተመለከተ

- ካህን፡- ክህነት በእግዚአብሔር በሰው መካከል ሆኖ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ ካህን ይባላል። አገልግሎቱ መሥዋዕትን በመሠዋትና ጸሎትን በመጸለይ ይፈጸማል። ካህን በማንኛውም ሃማኖት አለ።

የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት በገጽ 178

2. ክህነትን በተመለከተ

- ትምህርተ አበ ነፍስ በተባለው መጽሐፍም ላይ ካህን ለማለት ተክህነ አገለገለ ካለው ከግእዝ የወጣ ቃል ነው። ፍቺውም አገልጋይ ማለት ነው ይህም ሲሆን አንድ ሰው ሥልጣነ ክህነትን ከተቀበለ ጀምሮ ራሱን ለሕዝብ የሚያስገዛ የሚያገለግል ማለት ነው በማለት ተተርጉሞ እናገኘዋለን።

2. ክህነትን በተመለከተ

- የቤተክርስቲያን ሥራዋ ምእመናንን ማንጻትና ማጽናት ነው። ይህንም ቅዱስ ሥራዋን በተለዩ መሣሪያዎቿ በካህናት ትፈጽማለች። እነርሱም ሥልጣንን መብትን ከካህናት አለቃ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበሉ ናቸው። (ኤፌ ፬፥፲፩-፲፪) እነዚህም የቤተክርስቲያን አገልጋዮች የተባሉት ካህናት በቤተክርስቲን መራጭነት ተመርጠው በአንብሮተ እድ ተሸመው መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ከሕዝብነት ተራ ወጥተው ለዚህ ግብር ብቻ የተወሰኑ ናቸው። (ትምህርተ አበ ነፍስ ፴፭)

2. ክህነትን በተመለከተ

- ካህን እግዚአብሔር ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጠረውን ዓለም የሚመግብ የሚያስተዳድርና የሚቆጣጠር ሹም ባለሙያ ነው። ይህ መንፈሳዊ የሆነ መጋቢ አስተዳዳሪና ተቆጣጣሪ የሆነ ሹም ዓለምን በፈጠረ በእግዚአብሀየር በፍጡራን መካከል ሆኖ የባለሟልነትና የአስታራቂነት ተግባር የሚፈጽም ልዩ ባለሥልጣን ነው። (ፎቆሮ ፭፥፲፱) (ሐመር ጎዳር /ታጎሣሥ ፳፻)

2. ክህነትን በተመለከተ

- ክህነት በሰውና በእግዚአብሀየር መካከል የሚፈጸም (እንደ ድልድይ የሚያገለግል) መንፈሳዊ አገልግሎት ነው። ምድራዊያን መሪዎችና ዳኞች ገንዘብ ሊያደርጉት የማይቻል ሰማያዊ ሹመት ነው። ቤተክርስቲያን ምእመናን የምትመግብብት የምታስተዳድርበትና የምትጠብቅበት ሁነኛ መስመር ክህነት ብቻ ነው። በምድር ላይ በሚፈጸም ምስጋና ጸሎትና ተልእኮ ቅዱሳን መላእክትን የሚያስመስል ለሰውና ለእግዚአብሔር የሚኖርና ፍቅር የሚገለጽበት መንገድ ነው።

2. ክህነትን በተመለከተ

- በእግዚአብሔር ፈቃድ ጥሪና ምርጫ ለሰው ልጆች ሁሉ በፍቅር የሆነ አገልግሎት መስጫ መሣሪያ ቢኖር ክህነት ብቻ ነው። ከምንም በላይ ክህነት ሊቀ ካህናት ኢየሱ ክስቶስን በመምሰል ራስን ዝቅ የሚያደርጉበት ስለ ቤተክርስቲያን ራስን ሳይሆን ሌሎችን ለመጥቀምና ለመጥቀምና ለማገልገል የሚጓዙት የሕይወት መንገድ ነው። (ማቴ ፲፩፥፳፱፥፳፰) ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርቲያን አንዱና የምስጢራት ሁሉ ማከናወኛ የሆነ ቁልፍ መሣሪያ ነው።

2. ክህነትን በተመለከተ

2.2 ሕዝባዊ ክህነት /ክህነት አበው ዘሕገ ልቡና

አማናዊው የሐዲስ ኪዳን ክህነት ከመጀመሩ በፊት ሀብት ምሳሌያዊ ጉዞዎችን ተጉዟል።

እነዚህም:- ክህነተ አበው ዘሕገ ልቡና

ክህነተ አበው ዘሕገ ኦሪት የሚባሉት ናቸው።

ከአዳም እስከ ሙሴ በሚደርሰው የሕገ ልቡና ዘመን /ዘመነ አበው/ የነበሩ አበው ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው የክህነትን አገልግሎት ፈጽመዋል። በዚህም አገልግሎታቸው እግዚአብሔርን በማስደሰት አምላካዊ በረከትንና ለጥያቄዎቻቸውም መልስን አግኝተውበታል።

2. ክህነትን በተመለከተ

- በዚያችም ቀን አዳም ከኤዶም ገነት ሲወጣ ለበጎ መዓዛ ነጭ ዕጣን ቀን ዓትና ልባንጃ ስንቡልም ጎፍረቱን በሸፈነበት ቀን በጥዋት ፀሐይ ሲወጣ አጠነ።

(ኩፋ ፭፥፭)

አቤልም ደግሞ ከበጎቹ መጀመሪያ የተወለደውንና ከሰቡት አቀረበ እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ። (ዘፍ ፬፥፬)

ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠዊያውን ሠራ፤ከንጹሕም እንሰሳ ሁሉ (ከንጹሕም ወፎች) ወስዶ በመሠዊያውም ላይ መሥዋዕትን አቀረበ እግዚአብሔር አምላክም መልካሙን መዓዛ አሸተተ " (ዘፍ ፰፥፳-፳፩)

2. ክህነትን በተመለከተ

እግዚአብሔርም ለአብራም ተገለጠለትና ይህችን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ አለው። አብራምም ለእርሱ ለተገለጠለት ለእግዚአብሔር በዚያ መሠዊያውን ሠራ። በዚያም በዚም ለእግዚአብሔር መሠዊያን ሠራ የእግዚአብሔንም ስም ጠራ። (ዘፍ ፲፪፥፯-፱)

በዚያም ለአምላኩ ለእግዚአብሔር መሠዊያውን ሠራ የእግዚአብሄርንም ስም ጠራ በዚያም ድንኳን ተከለ የይስሐቅም ሎሌዎች ጉድጓድ ማሱ። (ዘፍ ፳፮፥፳፭)

2. ክህነትን በተመለከተ

- ያዕቆብም በተራራው ላይ መሥዋዕቱን ሠዋ ወንድሞቹንም ጠራ እነርሱም በሉ ጠጡም በዚያም በተራራው አደሩ። (ዘፍ ፴፩፥፶፬)
- እስራኤልም ለእርሱ ያለውን ሁሉ ይዞ ተነሣ ወደ ዐዘቅተ መሐላም መጣ መሥዋእትንም ለአባቱ ለይስሐቅ አመላክ ሠዋ። (ዘፍ፵፮፥፩)

2. ክህነትን በተመለከተ

2.3 ነገረ ክህነት በሕገ አሪት

ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ ያለው ዘመን (ዘመነ አበው/ሕገ ልቦና) ሲፈጸም አምልተ እግዚአብሔር በተሻለ አደረጃጀትና የሠመረ ሥርዓት እንዲፈጸም ፈቅዶ እግዚአብሔር ሆነ።

በዚህ የሕገ አሪት ክፍለ ዘመን የአምልኮተ እግዚአብሔር ዋናው ፈጻሚና አስፈጻሚ የሆነው የክህነቱ ዘርፍ በልዩ መንገድ (ሁኔታ) ሲጠራና የክንውን መመሪያ ተቀብሎ ሥርዓተ ደብተራ አሪቱን ሲመራ እንመለከታለን።

2. ክህነትን በተመለከተ

- አንተ ወንድምህን አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይተህ በክህነት ያገለግሉኝ ዘንድ ወደ አንተ አቅርብ ፤ አሮንን የዐሮንንም ልጆች፣ ናዳብን፣ አብዩድንም፣ አልዓዛርንም፣ ኢታምርንም አቅርብ።" **(ዘፀ ፳፰÷፩) እንዲል**
- የክህነት አስጣጥ ምስጢሩንም በተመለከተ እግዚአብሔር ለሙሴ ተገቢውን መመሪያ ሲያስተላልፍ እናየዋለን። ይህም ክብረ ክህነትን የሚያጎላ የተሰጠውንም ልዩ ትኩረት የሚያሳይ ሥርዓተ ክህነት ዘሕገ ኦሪት ነው።

2. ክህነትን በተመለከተ

- እኔንም በክህነት እንዲያገለግሉኝ ትቀድሳቸው ዘንድ የምታደርግላቸው ነገር ይህ ነው። ነውር የሌለባቸውን አንድ ወይፈንና ሁለት አውራ በጎች ትወስዳለህ። ቂጣ እንጀራ፣ በዘይት የተለወሰ የቂጣ እንጎቻ፣ ዘይትም የተቀባ ስስ ቂጣ ከመካከልም ስንዴ ታደርጋለህ። በአንድ መሶብም ታደርጋቸዋለህ፤ ከወይፈኑና ከሁለቱ አውራ በጎት ጋር በመሶብ ታቀርባቸዋለህ፣ አሮንንና ልጆቹን ወደ ምስክሩ ድንኳን ደጃፍ ታቀርባቸዋለህ፤

2. ክህነትን በተመለከተ

- በውኃም ታጥባቸዋለህ ለብሶችን ወስደህ ለወንድምህ ለአሮን የነጭ ሐር እጅ ጠባብ ቀሚስ አልብስ መትከፍና ልብስ እንግድዓ ታለብሰዋለህ። ለእርሱም ልብስ እንግድዓውን ከልብስ መትከፍ ጋር አያይዝለት። አክሊልንም በራሱ ላይ ታደርጋለህ፤ የወርቁንም ቀጸላ በአክሊሉ ላይ ታኖራለህ። የቅብዓትንም ዘይት ወስደህ በራሱ ላይ ታፈሰዋለህ፤ ትቀባውማለህ።... የምስክሩም ድንኳን መሠዊያውንም እቀድሳለሁ፤ በክህነትን ያገለግሉኝ ዘንድ አሮንንና ልጆቹን እቀድሳለሁ።" (ዘፀ ፳፱÷፯—፳ ፡ ፵፩)

2. ክህነትን በተመለከተ

- በሊቀ ነቢያት ሙሴ ታላቅ ወንድም በሊቀ ካህናቱ በአሮን የተጀመረው የሕገ ኦሪት ክህነት እስከ ቀያፋና ሐና ድረስ ሳይቋረጥ ቀጥሎ ነበር።
- **ቅብብሎሽ**
- አሮንንና ልጁን አልዓዛርን ይዘህ በማኅበሩ ሁሉ ፊት ወደ ሆር ተራራ ላይ አምጣቸው፤ ከአሮንም ልብሱን አውጣ፤ ልጁንም አልዓዛርን አልብሰው አሮንም ወገኑ ይጨመር በዚያም ይሙት። “ **(ዘኍ ፳÷፳፫ - ፳፭)**

2. ክህነትን በተመለከተ

የአሮን ልጅ ሊቀ ካህናቱን አልዓዛር ሞተ በተራራማው በኤፍሬም አገር ለልጁ ለፊንሐስ በተሰጣቸው በጊብዓት መሬት (በሞተ ጊዜ) መሬት ቀበሩት። የዚያን ጊዜ የእስራኤል ልጆች የእግዚአብሔርን ታቦት ከእነርሱ ጋር ይዘዋት ሄዱ። ፊንሐስም እስከ ሞተና በቦታቸው በጊብዓት እስከ ቀበሩት ድረስ በአባቱ በአልዓዛር ፊት ሊቀካህናት ሆነ።" **(ኢያ ፳፬÷፳፫—፳፭)**

2. ክህነትን በተመለከተ

- ## 2.3.1 ተልእኮ
- ### ፩ ሊቀ ካህናቱን በተመለከተ
- በዓመት ፩ ቀን በምስክሩ ታቦት ላይ ወዳለው ወደ ስርየቱ መክደኛ ወደተቀደሰው ስፍራ ይገባ ነበር **(ዘሌ. ፲፮፥፪-ፍጻሜው)**። ይህን አስመልክቶ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ገልጾታል።
- ወደ ሁለተኛይቱ ክፍል ግን ሊቀ ካህናቱ ታጠኢአታቸውን ለማስተስረይ ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ የሚያቀርበውን ደም ይዞ፥ በየዓመቱ አንድ ጊዜ ብቻውን ይገባ ነበር።" **(ዕብ. ፱፥፯)**።

2. ክህነትን በተመለከተ

- በዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ መሠረት ሊቀ ካህናቱ በዓመት አንድ ቀን መግባቱ ብቻ ሳይሆን የሚገባበት ምክንያትም ተጠቅሷል። ይህም የሊቀ ካህናቱን ተግባር ያሳያል። ሊቀ ካህናቱ ኃጢአትን የማስተሰረይ ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን በዓመት አንድ ቀን የማስተሰረያውን ደምን ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባ የነበረው የራሱንና የሕዝቡን ኃጢአት ለማስተሰረይ ነበር **(ዘሌ. ፱፥፯)**።

2. ክህነትን በተመለከተ

- ይህም ለአማናዊው ሊቀ ካህናት ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ እንደነበር ሐዋርያው በዚሁ ምእራፍ አያይዞ አቅርቦታል። የአራቱ ሊቀ ካህናት በየዓመቱ አንድ ጊዜ ለስርየተ ኃጢአት የእንስሳቱን ደም ይዞ ወደ ውስጠኛይቱ ክፍል ይገባ ነበር። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በየዓመቱ መግባት ሳያስፈልገው ለስርየተ ኃጢአት ዓለም አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ ሥጋውን ቆርሶ፥ ደሙን አፈሰሰ። እንደ እነዚያ በየጊዜው ደሙን ማፍሰስ አላስፈለገውም። ስለዚህም ምሳሌነታቸው ተነፃፃሪነቱ በእጅጉ ያነሰ ነው።

2. ክህነትን በተመለከተ

- በተጨማሪም ሐዋርያው የሊቀ ካህናቱ ተግባር ስለ ኃጢአት መባንና መሥዋዕትን ማቅረብ መሆኑን ገልጸልናል (ዕብ. ፭፥፩)። ይህም አገልግሎት ከጸሎት የተለየ እንደማይሆን የታወቀ ነው። መባውንና መሥዋዕቱን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበው ኃጢአታቸውን ይቅር እንዲላቸው ከመጸለይ ጋር መሆኑ ከማንም ሊሰወር አይችልም።

- ፪ ካህናቱን በተመለከተ

- ካህናት በመጀመሪያይቱ ድንኳን በየጊዜው አገልግሎታቸውን ይፈጽሙ ዘንድ ዘወትር ይገቡ እንደነበር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ገልጿል (ዕብ. ፱፥፮)። የዘመነ ኦሪት ካህናት የዘወትር ተግባራቸውም፦

2. ክህነትን በተመለከተ

- - የሚቃጠልን የእህል ቍርባን (መሥዋዕት) በእግዚአብሔር ዘንድ በጎ መዓዛ እንዲሆን ማቅረብ፤ (ዘሌ. ፩፥፱፤ ፪፥፩-፲፫)።
- - በመሠዊያው ላይና በታች የመሥዋዕቱን ደም መርጨትና ማፍሰስ፤ (ዘሌ. ፫፥፪-፱)።
- - ስቡን፥ ላቱን፥ የሆድ ዕቃውን፥ ኩላሊቶች፥ የጕበቱን መረብ ማጤስ (ማቃጠል)፤ (ዘሌ. ፫፥፫-፲፪፤ ፬፥፯)።
- የሕዝቡን ኃጢአት ማስተስረይ፤ (ዘሌ. ፬፥፯፤ ፴፩፥፴፭፤ ፭፥፩-፲፱)።
- - የለምጽ ደዌን መለየትና ማንጻት (መፈወስ)፤ (ዘሌ. ፲፫፥፲፭)።
- - መንፈሳዊ ብይን (ፍርድ) መስጠት፤ (ዘሌ. ፳፯፥፩-፮፤ ዘዳ. ፲፯፥፰-፲፪)
- - የብሩን መለከት መንፋት፤ (ዘኍል. ፲፥፩-፲፩)

2. ክህነትን በተመለከተ

- ዕጣን ማሳረግና ሕመማንን መፈወስ፤ (ዘኍል. ፲፮፥፵፩-ፍጻሜው)

ታቦተ እግዚአብሔርን ማክበር (መሸከም)፤ (ኢያ. ፫፥፩-ፍጻሜው፤ ነገ. ፰፥፫)

- የሕዝቡን ጸሎት ማሳረግ፤ (፩ኛ ሳሙ. ፩፥፲፪-፲፱)

ነገሥታትን ቀብቶ ማንገሥ፤ (፩ኛ ነገ. ፩፥፴፪-፴፭)

የእግዚአብሔርን ቤት መሥራትና መጠገን፤ (፪ኛ ነገ. ፲፪፥፱-፲፯፤ ፳፪፥፫-፰)

- - ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ፤ (፪ኛ ነገ. ፳፪፥፰-፲፩)

ቤተ እግዚአብሔርን ከርኩሰት ሁሉ ማጽዳትና መጠበቅ፤ (፪ኛ ነገ. ፳፫፥፬)

የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማስተማርና መገሠጽ፤ (፪ኛ ዜና. ፳፬፥፳-፳፫፤ ነህ. ፰፥፩-፱)

- - ሥርዓተ ቤተ መቅደሱን ማክበርና ማስከበር፤ (፪ኛ ዜና. ፳፭፥፲፭-፳፰)

2. ክህነትን በተመለከተ

- ከሌዋውያን ጋራ ቅዳሴ ቤተ እግዚአብሔርን ማክበር፤ (ዕዝራ. ፮፥፲፯)
- - ስለ ሕዝብና ሀገር ድኅነት መጸለይ፥ መጾምና ማልቀስ፤ (ኢዩ. ፪፥፲፯)
- የካህናትን ማንነትና የሚጠበቅባቸውን በተመለከተ እግዚአብሔር በነቢዩ ሚልክያስ ላይ አድሮ እንዲህ ይላል
- ካህኑ ሁሉን የሚችል የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነውና ከንፈሮቹ ዕውቀትን ይጠብቁ ዘንድ ይገባቸዋል፤ ሕጉንም በልቡ ይመረምር ዘንድ ይገባዋል።" **(ሚል. ፪፥፯)።**

2. ክህነትን በተመለከተ

፫ ሌዋውያንን በተመለከተ

ሌዊ ከ፲፪ቱ ነገደ እስራኤል መካከል የአንዱ ስም ሲሆን ከሱ የተወለዱ ሁሉ በአባታቸው ሌዋውያን ተብለዋል። የስሙ ትርጓሜ “ይጠጋል” ማለት ሲሆን የእናቱ ስም ልያ፥ የአባቱም ያዕቆብ (እስራኤል) ነው። ሙሴና አሮን ራሳቸው ከዚህ ነገድ የተወለዱ ናቸው። የአሮን ልጆች ለክህነት ሲመረጡ ሌሎች የሌዊ ልጆች ግን ለተቀረው የእግዚአብሔር አገልግሎት ተለይተዋል። ስለ እስራኤል በኩር ልጆች ፈንታ ሆነው የተሰጡ ናቸው (ዘኁ. ፫፥፲፪)። የካህናቱን አገልግሎት የውስጥ፥ የሌዋውያኑን ደግሞ የውጭ ብሎ መግለጽ ይቻላል።

2. ክህነትን በተመለከተ

- ቅዱስ መጽሐፍ በካህናትና በሌዋውያን መካከል የነበረውን ልዩነት ሲገልጽ “ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ አሮን ካህናት እለ ቅቡዓን ወእለ ፍጹማን እደዊሆሙ ከመ ይኩኑ ካህናተ፤ በክህነት ያገለግሉ ዘንድ የተቀቡና እጆቻቸውን የተቀደሱ የአሮን ልጆች ስም ይህ ነው።” (ዘኍል. ፫፥፫)። “ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎሙ ንሥአሙ ለነገደ ሌዊ ወአቅሞሙ ቅድመ አሮን ካህን ወይትለአክዎ፤ እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው።” **(ዘኍል. ፫፥፭-፯)።**

2. ክህነትን በተመለከተ

- በዚህም መሠረት ስንመረምር የካህናቱ ሹመት በቃል ብቻ ሳይሆን በምሥጢራዊ አፈጻጸም በከበረው ዘይት ቅብዓትም እንዳለው እንረዳለን። የሌዋውያኑ ደግሞ መመረጣቸው በቃል ብቻ መሆኑን በተጓዳኝ እንገነዘባለን። ሌዋውያኑ የካህናቱ ተራዳኢዎች መሆናቸውንም እንዲሁ።
- የሌዋውያንን አገልግሎት በተመለከተ በዚሁ መጽሐፍ በሚገባ የሰፈረ ሲሆን ጥቂቶችን ተግባራት እንደሚከተለው እናያለን።

2. ክህነትን በተመለከተ

- የድንኳኑን ሥራ መሥራት (ማንጠፍ፥ መጋረድ፥ መትከል፥ መንቀል፥... የመሳሰሉትን)፤
- ሕገ እግዚአብሔርን መጠበቅና ማስጠበቅ፤
- የምስክሩን ድንኳን ዕቃ (ንዋያተ ቅዱሳት) መጠበቅ፤ (ዘኁል. ፫፥፯-፱)
- ማደሪያውንና ድንኳኑን፣ መደረቢያውን፣ የምስክሩን ደጃፍ መጋረጃ፣ የዐደባባዩን መጋረጃና በድንኳኑ ዐደባባይ በር ያለውን መጋረጃ መጠበቅ፤
- መቅደሱን (ውጭውን) መጠበቅ፤
- አሮንና ልጆቹ (ካህናቱ) መቅደሱንና የመቅደሱን ዕቃ ሁሉ ሸፍነው ከጨረሱ በኋላ ሰፈሩ ሲነሣ ንዋያተ ቅዱሳቱን ሳይነኩ መሸከም፤
- ድንኳኑንና ማንኛውንም ከድንኳኑ ጋር የተያያዘውን ዕቃ ሁሉ መሸከም፤ (ዘኁል. ፫፥፲፬-ፍጻሜው። ፬፥፭-፴፬)።

2. ክህነትን በተመለከተ

- በዜማ ዕቃዎች በመሰንቆና በበገና በጸናጽልም እያዜሙ የዝማሬ አገልግሎት መስጠት፤ (ሯኛ ዜና. ፮፥፲፯-፳፱፤ ሯኛ ዜና. ፲፭፥፲፯-፳፭፤ ሯኛ ዜና. ፳፭፥፩-ፍጻሜው)።

2. ክህነትን በተመለከተ

2.4 ነገረ ክህነት በሕገ ወንጌል

እንደሚታወቀው አንድ ሰው ለመዳን ከሚያስፈልጉት ነገሮች መካከል እግዚአብሔር ወዶና ፈቅዶ ለሰዎች ያደረገውን፣ በቅዱሳት መጻሕፍት የገለጠውንና ሰው ሆኖ የፈጸመውን እንዲሁም እርሱና ሐዋርያት ያስተማሩትን በምልዓት መቀበል (ማመን) የመጀመሪያው ነው።

2. ክህነትን በተመለከተ

- ዳሩ ግን ይህ ብቻውን በቂ ሆኖ አያድነውም። ከላይ የገለጽነው የድኅነት መሠረት ሲሆን ጣሪያና ግድግዳ ኖሮት ድኅነት ሙሉ እንዲሆን ያመነበትን (የተቀበለውን) እንደታዘዘው መፈጸም ይኖርበታል። በዚያ በነበረበት ውስጥ የታዘዙ ትእዛዛትን መፈጸምና ለእግዚአብሔር የድኅነት ጥሪ ተግባራዊ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል።
- መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃሉ ካስተማረውና በተግባርም ካሳየው መካከል ምሥጢራትን መፈጸም ግንባር ቀደሙ ነው።

2. ክህነትን በተመለከተ

- የእግዚአብሔር ጸጋ (ስጦታ) የሆነውን ድኅነት ገንዘብ ለማድረግ የግድ መፈጸም ያለባቸው ሦስቱ ምሥጢራት፦- ጥምቀት፥ ሜሮንና ቊርባንም ሆኑ ቀሪዎቹ አራት ምሥጢራት፦- ክህነት፥ ንስሓ፥ ተክሊልና ቀንዲል በአንድ ሰው የድኅነት ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያላቸው ናቸው። እነዚህ ምሥጢራትም የሚፈጸሙት በካህናት ሥልጣንና አገልግሎት ብቻ ስለሆነ ድኅነትና ነገረ ክህነት ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አላቸው ማለት ነው።
- በቅዱስ ወንጌል እንደተነገረው ያመነ መጠበቅ፥ በመንፈስ ቅዱስ መክበር (መቀደስ) እና ቅዱስ የሆነውን ቊርባን መቀበል አለበት።

2. ክህነትን በተመለከተ

- በዚህ ጊዜ ነው የሀብተ ወልድና፥ የስመ ክርስትና ባለቤት የሚሆነው ከላይ እንደገለጽነው የምሥጢሩ መጋቢዎች ደግሞ ከሐዋርያት ጀምሮ በመተካካት ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ የነበሩና እያገለገሉ ያሉ ካህናት ናቸው (፩ኛ ቆሮ. ፬፥፩፤ ማቴ. ፳፭፥፲፱-፳)። በዚህ መሠረት የካህናት አለቃ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሾማቸው ሐዋርያትና ተከታዮቻቸው ካህናት ድኅነትን ተቀብለው ለመላው ዓለም ሲያድሉ ኖረዋል፤ እያደሉም ነው። ያለ ምሥጢረ ክህነት የሚገኝ ድኅነት ስለሌለ አስተምህሮ በማሳመን፥

2. ክህነትን በተመለከተ

- በማጥመቅ፥ በማክበና ሥጋ ወደሙን በማደል ሰዎችን በማዳን ጉዞ ውስጥ ተኪ የሌለውን ሚና የተጫወተውና የሚጫወተው የክህነቱ ዘርፍ ነው። በታጠቢአት ደዌ ተሰነካክሎ ከተቀበለው የድኅነት መስመር ያፈነገጠውን በንስሓ መርፌ አክሞና ፈውሶ ወደቀደመ ሕይወቱ (የድኅነት ወደብ) የመመለሱ ተግባርም ተደጋግሞ እንደተገለጸው የክህነቱን አካላት የሚመለከት ነው። እንዲህ ከሆነ ዘንድ ድኅነቱ ያለ ክህነቱ ሱታፌ አማናዊ አይሆንም፤ ክህነቱም ከድኅነቱ መስመርና ዓላማ የተለየ (የወጣ) ተልእኮ የለውም።

2. ክህነትን በተመለከተ

- እግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም የመጣበትና ሰው የሆነበት ዓላማ የሰውን ልጅ ወደቀደመ ክብሩና ሀገሩ ለመመለስ ማለትም ለማዳን ነው። ከላይ እንዳየነውም ለዚህ ዐብይ ዓላማ መሳካት (ለመላው ዓለም መዳረስ) ሥልጣን ሰጥቶ የሾማቸው ካህናት በመሆናቸው ምሥጢረ ክህነት የምሥጢረ ሥጋዌ ዐቢይ ክፍል ሆኖ ጉልህ ሚናውን በመፈጸም ላይ ይገኛል።
- መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው በተደጋጋሚ ጽኑ በሆነ ቃል ኪዳን ለደቀ መዛሙርቱ ሥልጣነ ክህነትን ሰጥቷቸዋል። ይህን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ሲመሰክር እንዲህ ይላል።

2. ክህነትን በተመለከተ

- እኔም እልሃለሁ፤ አንተ ዐለት ነህ፤ በዚያች ዐለት ላይም ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ፤ የሲዖል በሮችም አይበረታቱባትም። የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የምትፈታው በሰማይ የተፈታ ይሆናል።” **(ማቴ. ፲፮፥፲፰-፳)።**
- እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር የምታስሩት በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈቱት በሰማይ የተፈታ ይሆናል” **(ማቴ. ፲፰፥፲፰)።**

2. ክህነትን በተመለከተ

- ይህንንም ብሎ እፍ አለባቸው፤ እንዲህም አላቸው፤ “መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ይሰረይላቸዋል፤ ይቅር ያላላችኋቸው ግን አይሰረይላቸውም” **(ዮሐ. ፳፥፳፪-፳፫)።**
- በዚህ መልክ ጸጋ ሆኖ የተሰጠው ሀብተ ክህነት በሐዲስ ኪዳን የምሥጢራት ማስፈጸሚያና ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚያስገባውን በር የሚከፍተው ቁልፍ ባለቤት ሆኗል።

2. ክህነትን በተመለከተ

- ከነዚህ ማስረጃዎች በተጨማሪ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የጳጳሳት የቀሳውስትና የዲያቆናትን የአሿሿም ሂደትንና የተሿሚዎች መስፈርትን አስፍሮልናል። **(፩ጢሞ ፫፥፩-ፍጻሜው ፣፭፥፱-፳፪ ቲቶ ፩፥፭-፯)።**
- ይህም የተጻፈው ምስጢረ ክህነት በቅብብል የሚቀጥል ስለሆነ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ በዘመኑ ሁሉ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ።(**ማቴ ፳፰፥፳**) በማለት የተናገረው ሐዋርያት በዚህ ዓለም ለዘላለም ሲያስተምሩና ሲያጠምቁ የሚኖሩ ሆነው ሳይሆን በእግራቸው ተተክተው እስከ ኀልቀተ ዓለም የሚነሡ ካህናትን ሁሉ የሚመለከት ነው።

2. ክህነትን በተመለከተ

- የአባቶቻችን ካህናት ሥልጣናቸው የሐዋርያት ሥልጣን ነውና።
- በዚህ የሥልጣን ቅብብሎሽ መሠረት ነው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ካህናትም አሁን ድረስ ያገለገሉትና እስከ ምጽአትም ድረስ የሚነሡ ካህናት የቤተክርስቲያንን ሥራ የሚሠሩት (የሚያገለግሉት)።

2. ክህነትን በተመለከተ

- የቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ መንበር በእስክንድርያ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ አንድም ጊዜ ሳይቋረጥ ሐዋርያዊ የሥልጣን ሽግግሩ እስከ ዘመናችን ደርሷል

2. ክህነትን በተመለከተ

- **በምን በምንስ ይሻራል?**
- **ማን ማንን ይሸራል?**
- በክህነቱ የማይገባ ሥራ የሠራ በማንኛውም ማዕርግ ያለ ካህን በቤተ ክርስቲያን ሊሻር ይችላል ይህንን ማድረግ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ነው። ይሁን እንጂ አፈጻጸምና ፈጻሚ አካል ስላለው ማንም እንደፈለገ ተነስቶ አንዱንም አንዱን የመሻር ሥልጣን የለውም።
- ክህነት መስጠትም ሆነ መሻር የጳጳሳት ማዕርግ ነው።
- ከዚያ በታች ያሉት የመሾምም የመሻርም ሥልጣን የላቸውም ቢያደርጉት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን መሻር ነው።

2. ክህነትን በተመለከተ

- ምንምንኳን አለቃ አያሌው የተማሩና ለቤተ ክርስቲያን የሚቆረቆሩ ቢሆኑም አንድ በቅስና ማዕርግ ያለ ሰው ማውገዝ አይችልም። ሌሎች አበው ጳጳሳት ባይኖሩና ከፓትርያርኩ ውጭ ሊገኝ የሚችለው አንድ ካህን ቢሆን እንኳን ሌላ አባት ስለ ሌለ ነው ይባል ነበር በርካታ ጳጳሳትና የሲኖዶስ አባላት እያሉ አንድ ካህን ብድግ ብሎ ፓትርያርኩን ይቅርና ቄሱንም ማውገዝ አይገባውም።

ክህነታዊ ግብር በካህኑ ቅድስና ላይ የተመሠረተ አይደለም።

ይህንን በቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ገላትያ ሰዎች በምዕራፍ 6÷5 ላይ እስመ ኩሉ ጸሮ ይጸውር፦ ሁሉም የራሱን ሸክም ይሸከማል ያለውን <u>በአንድምታው</u> ሲተረጉሙ የሚከተለውን ታሪክ አስቀምተዋል።

አንድ ገበሬ ካንድ ባለርስት ካህን መሬት ተቀብሎ ያርስ ነበር አንድ ቀን አገልጋዩን ካህኑን የሰጠውን እርሻ እረስ ብሎት ሲያርስ ድስት ሙሉ ወርቅ አገኘ ሂዶ ቢነግረው እኛ ፍሬውን እንጂ ወርቁስ ለባለ ርስቱ ለካህኑ ነው ሂደህ ለካህኑ ንገር አለው

- ካህኑ ግን ይንን ሲሰማ ለሰው ይግርብኛል ያጋራኛል ብሎ ፈርቶ ቆፍረው ወርቁን ሲያገኙት ያንን አገልጋይ በሰይፍ ገደለው። ደሙ ቢፈስበት ወርቁ ገል ጠጠር ሆነ። ያ ገበሬ አገልጋዩን እየፈለግ ቢመጣ ካህኑ ገድሎት አገኘ ከዚያ በኋላ ቤተ ክርስቲያን የማይሄድ ሥጋ ወደሙን በካህን እጅ የማይቀበል ሆነ። መልአክ መጥቶ የምታየው ነገር አለህና ወደ ቤተ ክረስቲያን ሂድ አለው። ቢሄድ ያንን ካህን ሰይጣን በእሳት አለንጋ ለጉሞ በእሳት ጅራፍ እየገረፈ ይዞት ሲሄድ ከቤተ እግዚአብሄር ሲደርስ ሲወርድለት

ሥራውን ሠርቶ ሲፈጽም እንደቀድሞው በእሳት ልጓም ለጉሞ፣ በእሳት አለንጋ እየገረፈ ጋልቦት ሲመለስ አይቶ ለካ ቅዱስ ጳውሎስ <<እስመ ኩሉ ፆሮ ይፀውር፡- ሁሉም የራሱን ሸክም ይሸከማል>> ያለው ይህ ነው ብሎ አድንቋል

ሥጋውን ደሙን አልቀበልም ላለው አንድ ቀን በህልሙ ከላይ ውሃው የሚመነጭበት ገደሉ የወርቅ ከታች ውሃው የሚከማችበት ገበታው የወርቅ ሁኖ አንድ እጅ እግሩ የቆሳሰለበት ሰው በወርቅ ማንኪያ እየጠለፈ እንካ ላጠጣህ ሲለው እርሱ ተጸይፎ እንቢ ሲል ምነው መፍለቂያውም ገበታውም ማንኪያውም በእጁ አልነካው ጠጣ እንጂ ሲለው አደረ።ይህም ምሳሌ ነው፡- የዉሃው መፍለቂያ የጌታችን ጎን ነው።

- ከታች መቀበያው ቤተ ክርስቲያን ናት
- ጽዋውና ማንኪያው ስልጣነ ክህነት ነው።
- እጅ እግሩ የቆሰለው ሰው የታጠቢአተኛ ካህን ምሳሌ ነው በጂ አይነካው ማለቱ ካህኑ ጸሎቱን ያቀርባል እንጂ ጎብስቱን ሥጋ መለኮት፣ ወይኑን ደመ መለኮት የሚያደርግ ራሱ ባለቤቱ ነውና።

ኑባበ. ፡ መለኩት ፡ ጎርንርዮስ ፡ ለለ ፡ ጥምቀት ፡
በሚናገረው ፡ በአራተኛው ፡ ድርሳኑ ፡ እኔም ፡
ክፉውንና ፡ በጎውን ፡ ሰው ፡ በሰምዕ ፡ ከንርሱ ፡
ከሀሳትን ፡ በሥለት ፡ ማጎቱም ፡ መለሎ ፡ ተና
ገረ ። ከእንርሱ ፡ አንዱ ፡ የወርቅ ፡ ሠለተኛው ፡
የብረት ፡ ሦስ ፡ በውስጣቸው ፡ የእንጨ ፡
ንኩሥ ፡ መልክ ፡ የተሠረጸባቸው ፡ ናቸው ።

ስምዕ ፡ በታሪኩመሰከሯውም ፡ ጊዜ ፡ የንጉሣዊ ውን ፡ ቅርጽ ፡ በማስገኘት ፡ በወረቅ ፡ ማኅ ተም ፡ በታሪኩመው ፡ መካከልና ፡ በብረት ፡ ማኅ ተም ፡ በታሪኩመው ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ የለም ። በኋላ ፡ ጊዜ ፡ በብረት ፡ ከታተመው ፡ ተለይቶ ፡ በወረቅ ፡ የታተመው ፡ እያታወ ቅም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መለየትስ ፡ የሚያስመ በት ፡ በሚኩበለውና ፡ በማያኩበለው ፡ መካ ከል ፡ ነው ። ለሥራ ፡ ግን ፡ በቅርቡ ፡ ልዩነት ፡ የለም ። ጳጳመኛ ፡ ምጣቤ ፡ የጉደለው ፡ ክህን ፡ እንደሰም ፡ መብረት ፡ ነው ። የሚነደው ፡ እሳት በክህንቱ ፡ ይመሰላል ፤ እሳቱም ፡ ሰሙን ፡ ያቀ ለጠዋል ፡ ለሕዝቡ ፡ ግን ፡ ያበራል ፡ ከብርሃኗ ፡ የተነሣ ፡ ፴ለሰማ ፡ እያከበረው ። ።

ስለዘሀች ፡ ትረክሚ ፡ ከሠለት ፡ ስዎች ፡ ሌላ ፡ ምሳሌ ፡ እናምጣ ፡ እንዴ ፡ ያማ ፡ እንዳ ፡ ክፉ ፡ ነው ። ሠለት ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ፈቀድ ፡ አለ ፡ቸው ፡ ፈቃዳቸውም ፡ አንድ ፡ ነው ። ስንጉሡም ሠለት ፡ መኳንንት ፡ አለ ፡ አንዴ ፡ ያማ ፡ አንዴ ፡ ክፉ ፡ ነው ። ያገ ፡ ስው ፡ ከንጉሡ ፡ ፈቃዱን ፡ ያለጽምለት ፡ ዘንድ ፡ ክፉውን ፡ ጸኖ ፡ ማለያው ። ክፉውም ፡ ስው ፡ እንያዚህ ፡ ፈቃዱን ፡ ያለጽምለት ፡ ዘንድ ፡ ያጉን ፡ ጸኖ ፡ ማለያው ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ አዋቂ ፡ ነው ። የሠለቱንም ፡ መኳንንት ፡ ሥራቸውን ፡ ያወቃል ።

መኳንንቱ ፡ ስለ ፡ ሣዳጃቸው ፡ ንጉሡን ፡ በማለ ዴ.ት ፡ ነ.ዜ ፡ የሄንኛውን ፡ ፊ.ቃድ ፡ በክፋው ፡ ዶኛ ፡ እድ ፡ ፈሐረስ ። የዶኛው ፡ ክፋ.ት ፡ ፊ.ቃ ዱን ፡ እልከለከለበትም ፡ የክፋውን ፡ ፊ.ቃ ድ ፡ በሄን ፡ ዶኛ ፡ እድ ፡ እልፈሔረስም ፡ ስለ፡ሰ ፡ ክፋ.ት ፡ የዶኛው ፡ ሄንት ፡ እልጠሩመውም ፡ ቢ.ቀበልና ፡ በ.ጠቀምም ፡ እንጂ ! እማዘ.ብ ሐረ፡ ፡ ያሠ.ቃል ።

ፍት ነ አን 9፡342

ዘኂቱ ፡ ወዘይትናገር ፡ ቃለ ፡ ጎሡመ ፡ ላዕለ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ጥሁ ፡ አበሰ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢሰማዕክሙኑ ፡ ዘይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢትት ናገሩ ፡ ነገረ ፡ አኮየ ፡ ላሶለ ፡ አግልክት ። ወኢይ ምሰልክ ፡ ዝንቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘተብህለ ፡ በእንተ ፡ ጣዖታት ፡ አላ ፡ በእንተ ፡ ካህናት ፡ ወፈጻሕት ፡ ዘተብህለ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ “አግልክት ፡ እን ትሙ ፡ ወይቲቅ ፡ ልዑል ፡ ኮልክሙ ፡ ትብሙዩ” ወክዕበ ፡ ይቤልሙ ፡ ሙሴ ፡ ለሕዝብ ፡ አለ ፡ ተቃወምዎ ፡ ለሙሴ ፡ እት ፡ ላዕሌየ ፡ ዘታንጕረ ጕሩ ፡ አላ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ። ወሶበ ፡ ኮን ፡ ዘይቤሎ ፡ ለሕዝባዊ ፡ አ ፡ ሰሎዕ ፡ አሙ ፡ ወብድ ፡ ኢይድኅን ፡ አምኑንኔ ፡ አሰሙ ፡ ዝንቱ ፡ ትዕይርት ፡ ይክውን ፡ ላዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ ወአፍኬ ፡ ይክውን ፡ ቃለ ፡ ዘይቤ ፡ ላሶለ ፡ ኤጲስ ቆጶለ ፡ በእንብሮ ፡ አይሁ ፡ ዘወሀበክሙ ፡ እግዚ አብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፮ ፥ በኢያሱም ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ቃል ፡ የሚናገር፡ እነሆ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በደለ ። እግዚአብሔር በእግልክት ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ነገር ፡ አትናገሩ ፡ ያለውን ፡ አልሰማችሁምን ? ስለ ፡ ጣዖታቱ ፡ ይህ ፡ ት·እዛዝ ፡ የተባለ ፡ አይምሰልህ ። ስለከሀዲ·ና ፡ ስለዳኞች ፡ ስለእንርሱ ፡ የተባለ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ “እናንተም ፡ ሁላችሁ ፡ እግልክትና ፡ የልዑል ፡ ልጆች ፡ ትባላላችሁ” ። (መዝ ፡ ፹፪ ፡ ፮) ። ዳግመኛም ፡ መሴ ፡ የሚቋቋመውን ፡ ሕዝብ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ የምታንጐራጕሩ ፡ እያደላችሁም ፡ በእግዚአብሔር ፡ እምላክ ፡ ላይ ፡ ታንጐራጕራላችሁ ፡ እንጂ ። (ዘጕሌ ፡ ፲፮ ፡ ፲፭) ። አላቸው ። ሕዝባዊውን ፡ (ጨዋውን) ፡ አንተ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ አንተ ሰነፍ ፡ የሚለው ፡ ክቅጣት ፡ የማይድን ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ ተማጸጽት ፡ በክርስቶስ ፡ ላይ ፡ ነውና ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በሰጣችሁ

በኤጲስቆጶሱ ፡ ላይማ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ የተናገረ ፡

እንዴት ፡ ይሆን ? ።

ፍት ነ አ9፡313

ሲኖዶስ እያለ ሌላ ግለሰብ በክህነታዊ ጉዳይ መመሰን አይችልም

3.ትምህርታቸውን በትንቢት ላይ ብቻ መመሠረት/ማመካኘት

- እነዚህ አካላት ለሐሳባቸው የሚሆን ጥቅስ ሲያጡ እንደ ጥቅስ የሚያቀርቡት ምንጩ ያልታወቀ፣ ያለጠረጋገጠና ለሌላ ምሥጢር የተነገረውን ትንቢትን ነው።
- ትንቢት ምንድነው?
- ለምን ዓለማ ይነገራል?
- የነቢያተ ጽድቅና የነቢያተ ሐሰት መለያቸው ምንድነው?
- የመረጃ ነቢያትስ?

4. የበረኻ አባቶች መልእክት

- በዚህ ዙሪያ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ምን ይላል?
- የበረኻ አባቶችስ ካሉ የሚገለጹት ለነማን ነው?
- ሰው በረኻ ወድቆ የሚጸልየው ለምን ዓላማ ነው?
- የበረኻ አባቶች የሚባሉት የት የሚኖሩ ናቸው (ውቤ በረኻ) ወይስ ማኅበረ ሥላሴ?
- ከመልእክቶቻቸው ምንያህሉ ተፈጸሙ ምን ያህሉ ሳፈጸሙ ቀሩ?

- የተባህትዎን አኗኗር በተመለከተ ቤተ ክርስቲያን የታወቀና ግልጽ አስተምህሮ አላት
- ከተባህትዎ/ከብህትውና አስቀድሞ ምናኔ አለ ያለ ምናኔ ብህትውና ሚባል ነገር የለም።

ሀ. ምናኔ ማለት የዚህን ዓለም ክብር፣ ተድላና ደስታ፣ ሥልጣንና ዝና፣ መብል መጠጡን ማማር ማጌጡን ንቆ፤ ፍቅረ ዘመድን ታግሦ፣ ከዘመድ ባዳ፣ ከሀገር ምድረ በዳ ይሻለኛል ብሎ ወጥቶ በሥርዓተበ ገዳም ተወስኖ ገዳሙ የቆመውን ቁረጥ የወደቀውን ፍለጥ ቢለው ሁሉንም እሺ በጄ ብሎ በታዘዙበት ሁሉ በቅንነት ማገልገል፣ የአበውን እግራቸውን ልብሳቸውን እያጠቡ ባሪታ እየደፉ በረከት ሲቀበሉ መኖር ነው

ለ. ብሀትውና ማለት፡- ደግሞ ከላይ እንዳየንው ዐሥር ዐሥራ ሁለት ዓመት፤ ዐሥራ አምስት ሀያ ዓመት ረድቶ ሲደክም የወንዶች ገዳም የሆነ እንደሁ አባቶች ተሰብስበው ሂደው አባታችን እስከዛሬ ድረስ በጉልበትህ ረዳኸን ከእንግዲህስ ወዲህ ተባህተዎ ይዘህ በበዓት ተከተህ ከሰው ተለይተህ በጸሎትህ እርዳን ይሉታል፤ ይህንን ተቀብሎ ሲኖር ከሰው አይገናኝምና ባህታዊ ይባላል።

- ገዳሙ የእናቶች ገዳም የሆነ እንደሆነ እናቶች ተሰባስበው ሂደው እናታችን አስከዛሬ ድረስ በመፍጨት በመቁላት ዳቤ በመጋገር፣ በመውጣት በመውረድ በጉልበትሽ ረዳሺን ከእንግዲህስ ወዲህ ከሰው ተለይተሽ፣ በበዓት ተከተሽ በጸሎትሽ እርጂን ይሏታል ይህንን ተቀብላ ስትኖር ባህታዊት መባል ትጀምራለች እንጂ አንድ ሰው ስለመነኰሰ ብቻ ወይም ስለመነነ ገዳም ስለገባ ብቻ ባህታዊ አይባልም ገዳም ገብቶ በጉልበቱ ገዳሙን ሳረዳ ተባህተው እይዛለሁ የሚለውን ቀጥተው ያስወጡታል።

5.ቴዎድሮስ ይመጣል ስለሚሉት

- አንድ ክርስቲያን ነቅቶ ተግቶ መጠበቅ ያለበት ማንን ነው?
- ቴዎድሮስ የሚመጣው በመቸ ዘመን ነው?
- ሲጀመር ቴዎድሮስ ስንት ነው?
- ለሸዋ ኤረር ተራራ
- ለደቡብ ወሎ ደንቆሮ ጫካና ምስካበ ቅዱሳን
- ለሰሜን ወሎ ለላስቶች አቡነ ዮሴፍ/ለመቄቶች ዋሻ
- ለጎንደር ሱዳን
- ለጎጃም አዳማ ተራራ፣ ለደቡብ
- ለሀረር ወዘተ ሌላ ነውን

- ምንጮቹስ ምን ያህል አስተማማኞች ናቸው?
- ቴዎድሮስ የሚመጣስ ከሆነ ሥራ ፈት ሁነን መጠበቅ ይገባል?
- እስካሁን ራሳቸውን በዚህ መልኩ መጠን በማለት ያስተዋወቁ
- እነ ይሁዳ ዘገሊላ፣ ቴወዳስ ዘግብጽ፣ ሲሞን መሠርይ፣ በዐፄ ዘድንግል ጊዜ የተነሳው እነ ዘክርስቶስ በአቡነ ገብርኤል ጊዜ ክንፍ አለኝ እያለ ወሎ ላይ ያጭበረብር የነበረው፤ ኤልያስ መጣ እያሉ ብዙዎች የሚያቀነቅኑለት ሐሳዊ ተጠቃሾች ናቸው
- ቴዎድሮስ የሚነግሠው

6. የመዳኛ ምልክት

- አንድ ክርስቲያን ተግቶ እንዲፈልው የታዘዘው መዳን ከምንድን ነው?
- ለመዳንስ የተሰጡ ምልክቶች የትኞቹ ናቸው?
- የሚያድኑትስ ከምንድን ነው?
- የቀስተ ደመና እና የሰንደቅ አላማ ተዛምዶ እስከምን ድረስ ነው? ይህስ የተሰጠ ለኢትዮጵያ ብቻ ነውን?
- በምልክቱ ውስጥ የሚገኙ አርማወችንስ ወሳኙ አካል ማነው?
- የተወሰኑ ቃላት ብቻ የመዳን ምክንያት የሆናሉ የሚለው አስተምህሮ ከየት የመጣ ነው?
- ኃይል ይሆናሉ የተባሉትን ቃላትንስ ለይቶ ያወጣቸው ማነው
- በዋናነት ለምልክት የሚጠቅሱላቸው ሕዝቅኤል ምዕራፍ 9፡ ነው።።

- እርሱም፦ እያንዳንዳቸው የሚያጠፋ መሣሪያን በእጃቸው ይዘው ከተማይቱን የሚቀሥፉ ይቅረቡ ብሎ በታላቅ ድምፅ በጆሮዬ ጮኸ።
- እነሆም፥ እያንዳንዳቸው አጥፊውን መሣሪያ በእጃቸው ይዘው ስድስት ሰዎች ወደ ሰሜን ከሚመለከተው ከላይኛው በር መንገድ መጡ፤ በመካከላቸውም የበፍታ ልብስ የለበሰ የጸሐፊም ቀለም ቀንድ በወገቡ የያዘ አንድ ሰው ነበረ። እነርሱም ገብተው በናሱ መሠዊያ አጠገብ ቆሙ።

- የእስራኤልም አምላክ ክብር በበላዩ ከነበረበት ኪሩብ ተነሥቶ ወደ ቤቱ መድረክ ሄዶ ነበር፤ በፍታም የለበሰውን የጸሐፊውንም ቀለም ቀንድ በወገቡ የያዘውን ሰው ጠራ።
- እግዚአብሔርም፦ በከተማይቱ በኢየሩሳሌም መካከል እለፍ፥ በመካከልዋም ስለ ተሠራው ርኩሰት ሁሉ በሚያለቅሱና በሚተክዙ ሰዎች ግምባር ላይ ምልክት ጻፍ አለው።
- እኔም እየሰማሁ ለሌሎቹ፦ እርሱን ተከትላችሁ በከተማይቱ መካከል እለፉ ግደሉም፤ ዓይናችሁ አይራራ አትዘኑም፤

- ሽማግሌውንና ጕበዙን ቄንጆይቱንም ሕፃናቶቹንና ሴቶቹን ፈጽማችሁ ግደሉ፤ ነገር ግን ምልክቱ ወዳለበት ሰው ሁሉ አትቅረቡ፤ በመቅደሴም ጀምሩ አላቸው። በቤቱም አንጻር ባሉ ሽማግሌዎች ጀመሩ።
- እርሱም፦ ቤቱን አርክሱ፥ በተገደሉትም ሰዎች አደባባዮችን ሙሉ፤ ውጡ አላቸው። እነርሱም ወጥተው በከተማይቱ ገደሉ።
- ሲገድሉም እኔ ብቻዬን ቀርቼ ሳለሁ በግምባሬ ተደፍቼ፦ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ወዮ! መዓትህን በኢየሩሳሌም ላይ ስታፈስስ የእስራኤልን ቅሬታ ሁሉ ታጠፋለህን? ብዬ ጮኽሁ።

- እርሱም፦ የእስራኤልና የይሁዳ ቤት ኃጢአት እጅግ በዝቶአል ምድሪቱም ደም፥ ከተማይቱም ዓመፅን ተሞልታለችና፤ እነርሱም፦ እግዚአብሔር ምድሪቱን ትቶአታል እግዚአብሔርም አያይም ብለዋል።
- እኔም ደግሞ በዓይኔ አልራራም አላዝንምም፥ መንገዳቸውንም በራሳቸው ላይ እመልሳለሁ አለኝ።
- እነሆም፥ በፍታ የለበሰው የቀለም ቀንድም በወገቡ የያዘው ሰው፦ ያዘዝኸኝን አድርጌአለሁ ብሎ በቃሉ መለሰ።

ሕዝ፡ 9÷1-11

7.ዋናው የትምህርታቸው መሠረት ራእይ ነው

- ራዕየ ዮሐንስ እንዴት ይተረጓማል?
- መሠረታዊ መልእክቱ ምንድነው?
- እግዚአብሔር ለዮሐንስ ይህንን ራእይ ለምን ገለጸለት?
- ራእይ በቀጥታ የተነገረላቸው ሀገራት እነማን ናቸው?

8.ፍርድ ምንድነው

9.ክርስቲያኑን ሳይቀር የነሱን ምልክት ካልያዘ ማጥፋት

10.ስለ አብያተ ክርስቲያናት ያላቸው አስተምህሮ

- በየሀገረ ስብከቱና በየወረዳው
- ሰው የሚተርፈው በዕገሌና በዕገሌ ደብር ብቻ ነው በማለት አብያተ ክርስቲያናትን ማበላለጥ
- ስንቅ ማሰባሰብ
- ቤተ ክርስቲያን የነፍስ መዳኛ ሁና ሳለ እንደ ሥጋ መዳኛ ማስተማር

11.ስለኢትዮጵያ ያላቸው አስተምህሮ

12.ዋና ዋና ጥቅሶቻቸውና አጋዥ መጻሕፍቶቻቸው